የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ ጥር ፲፬ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 13
ADDIS ABABA 22nd January, 2010

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፮/፪ሺ፪ ዓ.ም

ለኢትዮጵያ ቱሪዝም ዘላቂ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ ለማግኘት ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተፈረመው የፋይናንስ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፭ሺ፩፻፺፰

CONTENTS

**Proclamation No. 666/2010**

International Development Association Financing Agreement for Ethiopian Sustainable Tourism Development Project Ratification Proclamation Page 5198

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፮/፪ሺ፪

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ቱሪዝም ዘላቂ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፳፫ሚሊዮን፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሃያ ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ ብድር የሚያስገኘው የፋይናንስ ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. በሴፕቴምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፱ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፬ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና /፲፪/ መሠረት እንደሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ቱሪዝም ዘላቂ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ ለማግኘት ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተፈረመው የፋይናንስ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፮/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 666/2010.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 23,600,000 SDR (twenty three million six hundred thousand SDR) for financing Ethiopian Sustainable Tourism Development Project was signed in Addis Ababa on the 16th day of September 2009;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Represent - atives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement at its session held on the 12th day of January, 2010;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Ethiopian Sustainable Tourism Development Project Ratification Proclamation No.666 /2010."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. በሴፕቴምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፱ በአዲስ አበባ የተፈረመው የፋይናንስ ስምምነት ቁጥር 4624-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፋይናንስ ስምምነቱ የተገኘውን ፳፫ሚሊዮን፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሃያ ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ በፋይናንስ ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፲፬ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Financing Agreement credit No. 4624ET signed in Addis Ababa on the 16th day of September 2009 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 23,600,000 SDR (twenty three million six hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of January , 2010**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**